# እኔና ፍራንክፈርት ጀርመን

## በአዲስ ተስፋ

የአገሬ ሰው ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው ይላል እውነትም ነው። በአገራችን ስለሚካሄደው ፖለቲካዊም ሆነ ማህበራዊ ለውጥ ለመተቸትም ለመደገፍም በቅርብ መረጃዎችን መያዝና በተጨባጭ መጻፍ ወይም መናገር ለሁሉም ይጠቅማል። በአጠቃላይ አመለካከቱ ከጅዋር መሃመድ ጋር ባልስማም ከሰሞኑ በሰጠው ቃለመጠይቅ የተጠቀመበት አንድ አገላለጽ ትኩረቴን ሳበው።” ጎማው በተነፈሰ ወይም ፍሬኑ በማይሰራና በወላለቀ መኪና ሾፌር መቀያየር ምንም ዋጋ የለውም። አስቀድሞ ጎማውም መሰራት ፍሬኑም መስራት ባጠቃላይ መኪናው ጤነኛ መሆን አለበት” ሲል የዶክተር አብይን መንግስት መቀየር ያለበት ሲስተሙ ነው በማለት በአግድሞሽ ተናግሯል። እንግዲህ ጃዋር ከጠቅላይ ሚንስትሩ በቅርብ ርቀት ሆኖ የታዘበው ስለሚሆን እውነትነቱን በሂደት ነው የምንመለከተው። ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ ነውና በዚህ ረገድ አክቲቪስቱን የምቃወምበት ወይም የምደግፍበት መሰረት የለኝም። ነገር ግን ዶክተር አብይ ወደ ፊት እያመጣቸው ያሉትን ታዋቂና ጠንካራ ሰዎች ሲስተሙ ሳይለዎጥ ምንም አይነት ሾፌር መቀያየር ዋጋ የለውም ከሚለው ሃሳብ ጋር እስማማለሁ። ሌላው የአክቲቪስት ጃዋር አተያይ ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ የሆነብኝ ጎማው መሰራቱን ፍሬኑ መጠገኑን በአጠቃላይ የሲስተም ለውጥ እንዲኖር ከፈለገ በኋላ የኢህአዴግ ስርዓት እንዳይፈርስ መፈለጉ ነው። እንዲያውም በዚህ አቅጣጫ ጠቅላይ ሚኒስተሩ ሊበራል ሆነው እያለ አቢዮታዊ ዲማክራት ነኝ ማለታቸው ሙልጭ ያለ ውሸት ነው ብሏል። በዚህም የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ መውደቅ እንደሌለበት ያ ከሆነ ፈደረሽኑ መፍረሱ እንደሆነ  የፈደሬሽኑ መፍረስ ደግሞ አገሪቱን እንደሚበታትናት ያለውን ስጋት በግልጽ አስቀምጧል። ስለዚህ የጃዋር ፖለቲካዊ አመለካከት ኢህአዴግ በሰራት በጎሳና ቋንቋ የተበታተነች አገር ወሳኝና ተሰሚነት ያለው አክቲቪስት ሆኖ መኖር ነው።ለማንኛውም አሁን አላማየ ጃዋርን መቃወም ወይም መደገፍ አይደለም ነገርን ነገር ያነሳዋል ሆኖብኝ እንጂ። ነገር በዓይን ይገባል እንዲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በዩቱዩብ ወይም በቴሌቪዥን በማያቸው መልእቶቻቸው ከምተቻቸው ወይም ከምደግፋቸው ለምን በአካል ተገኝቼ የህዝቡን ሁኔታም የእርሳቸውንም እቅድና ንግግርም አልመለከት ? አጋጣሚውን ካገኘሁም ጥያቄዎች እጠይቃለሁ ብየ ወደ ፍራንክፈርት ጀርመን ለመሄድ አቀድሁ። በኔዘርላንድስ ወደ ተከፈተው አዲስ የኢትዮጵያ ቆንጽላ ጽፈትቤትም ደውየ መረጃ ጠየቅሁ። አዲስ ተስፋ እንደምባል የሚቻል ከሆነ ፍራንክፈርት መሄድ እንደምፈልግና የሚያስፈልግ ምን እንደሆነ ማብራሪያ ከጠየቅሁና አስፈላጊውን መረጃ ካገኘሁ በሁዋላ ኦክቶበር 30 ከምሽቱ 11 ስዓት ከሌሎች 44 ሰዎች ጋር ሆነን ወደ ፍራንክፈርት በአውቶቡስ አቀናን።የደረስነው ከንጋቱ 6 ሰዓት ቢሆንም ስታዲየሙ የሚከፈተው ከጧቱ 10 ሰዓት በመሆኑ እና ፕሮግራሙ የሚጀመረው ከቀኑ 1 ሰዓት መሆኑ ስለተነገረን ከተማ ዞር ዞርን እያልን ቆየን።ጥያቄ የመጠየቅ ፍላጎት ቢኖረኝም ጥያቄ የመጠየ እድል ማግኘት የተበላ እቁብ መሆኑን ለማረጋገጥ ጊዜ አልዎሰደብኝም።

## የብሽሽቅ ፖለቲካና የሶስት ባንዲራ ትውልድ!

በመሰረቱ የፍራንክፈርቱ የጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ ንግግርም ሆነ አጠቃላይ የፕሮግራም ይዘት ብዙ ነገሮችን እንድመለከት አድርጎኛል። በመጀመሪያ ደረጃ ማንም ሰው የሚጠብቀው ሁለት ባንዲራዎችን ነው። አንደኛው አሁን የሀገሪቱ መንግስት በህግ የተቀበለውንና የሚመራበትን ሁለተኛው ደግሞ ህዝቡ ይህ ባንዲራ አይዎክለንም ስለዚህ የመንግስት አርማ የሌለበትንና በብዙዎች ዘንዳ የሚታውቀውን አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ  ቀለማት ። ብዙዎች ምናልባትም በፍራንክፈርቱ በነበረው የተቀነባበረ አሻጥር ሊቆጩና ሊበሽቁ እንደሚችሉ እረዳለሁ። በተለይም የካሜራማኑ ፎከስ እጅግ አሳፋሪ ነበር። ህዝቡ በተቀመጠበት ግራና ቀኝ የተቀመጠውና አብዛኛው ህዝብ የያዘው ባንዲራ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ብቻ ሆኖ እያለ በስክሪኑ የምንመለከተውና ረዥም ሰዓት የሚታየው ከ25% በታች የሆነ ህዝብ የያዘው የአነግ አርማ ነበር።የመድረክ አዘጋጆች በዚህ ሻጥር የሉበትም ለማለት አንዳችም ምክንያት የለም። እንግዳው የአገር መሪ ሆኖ እያለ አገርንና በንዲራን ከፍ ማድረግ ሲገባ ጎሳዊ ማንነትን ለማገዘፍ በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የእኛ ነገድ ነው ለማለት ምንም የማያውቁ ወጣቶችን በመጠቀም የሌላውን ስነ ልቦና ለመስለብ መሞከር ታናሽነት ብቻ ሳይሆን ፖለቲካው ባቃት ማነስም ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተወካይ ካደረጉት ልብ የሚነካ ንግግርና ቡራኬ በኋላ የተናገሩት የእምነት አባቶች ንግግርም ዓላማውና ሊያመጣ የተፈለገው ውጤት ግልጽ አይደለም። ኦሮምኛ ለምን ተነገረ አይደለም ህጋዊ መስረት ግን አልነበረውም። እስላሙ በኦሮምኛና አማርኛ፣ ፕሮቴስታንቱ በትግሪኛና አማራኛ ፣ዋቄፈታው በኦሮምኛ ፣ አብዛኛው የመድረክ ዝግጅት በኦሮምኛ አብዛኛው ዘፈን በኦሮምኛና ነገሮች ሁሉ አንድነት አንድነት ሳይሆን ክፍፍልን የሚሰብኩ ነበሩ። በተለይም ደግሞ አባገዳው ያደረጉት ንግግርና ቡራኬ ሌሎች የእምነት አባቶች ከደረጉት  ንግግር ባጠቃለይ የበለጠ ጊዜ መሰጠቱ አስልች ብቻ ሳይሆን ወዴት እየሄድን እንዳለ የሚያሳይ አሳሳቢ ክስተት ነበር። የጀርመን ማርሽ ባንድ የኢትዮጵያን ማራኪነትና ታላቅ ህዝብነት ለማሳየት ያደረገው ሙከራም ፈጽሞ ትኩረት ተነፍጎት ነበር። ምክንያቱን መገመት በጣም ቀላል ነው። የአነግ አርማ አልነበረውም። የማርሽ ባንዱ መሪ የሚያምር የኢትዮጵያን ባንዲራ ስካርፕ በአንገቱ ጠምጥሞ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ያደርጉት የነበረው ስታዲየሙን የመዞር እንቅስቃሴ ማራኪ ብቻ ሳይሆን የተለየ ኢትዮጵያዊ መስህብ ነበረው። አስቀድሞ የገዥው ፓርቲ አርማ ያለበት የሀገሪቱ ስንደቅዓላማ በስታዲየሙ በሮች ሁሉ ጎላ ብሎ ይታይ የነበረ ቢሆንም በሁዋላ ግን የአነግን አርማ ለማጉላት ተሞክሯል። ቢሆንም የሚበዛው  የኢትዮጵያን ባንዲራ የያዘውና ኢትዮጵያ የሚለው ነበር። ሌላውና ፈጽሞ ሊገባኝ ያልቻለው መድረኩ በአብዛኛው በሚባል መልኩ ይመራ የነበረው በኦሮምኛ መሆኑ ነው። በእርግጥ የአማርኛም የመድረክ መሪ ነበር። መመራት የነበረበት በአማርኛና በአንድ የውጭ ቋንቋ ማለትም በጀርመንኛ ወይም በእንግሊዘኛ ነበር።ኦሮምኛ ለምን ጎልቶ እንዲዎጣ እንደተፈለገ ባይገባኝም በምላሹ በተለይም የኦሮምኛ ዘፈኖች በብዛት ከመድረኩ በመለቀቃቸው ግራ የተጋባ ሌላ እዚያው ከመድረክ ያለ ሰው ያለ ለማስመሰል አንዳንዱ የቴዲ አፍሮ ዘፈኖች

መለቀቃቸውም የበለጠ በሴራ የተተበተበ መንድረክ እንደነበር ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ይህ የመበሻሸቅ አይነት እንድምታ ያለው አካሄድ በተለያዩ ሰዎች ሳይሆን በዚያው በአንድ የመድረክ መሪ ይቀነባበር ነበር። ኢትዮጵያ ጎላ ብላ ስትተረክ የኦነግን አርማ የያዙ ሰዎች ጸጥ ይሉ ነበር።የቴዲ አፍሮ ዘፈን ሲከፈት የኦነግን አርማ የያዙ ወጣቶች ሃጫሉ ፣ ሃጫሉ በማለት ለመጮህ ሙከራ ያደርጉ ነበር።ይህ ሁሉ እንቅስቃሴ ስብሰባው የተዘጋጀበትን መሪ ሃሳብ " በአንድነት እንነሳ ነገንም እንገንባ" ን ተጻራሪና አፍራሽ ነበር። እስካሁን ድረስ ጠቅላይ ሚንስቴር አብይ በግብጽና ፈረንሳይ ያደረጉት ንግግር እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ኩራት እንዲሰማኝ አድርጎኛል። ኢትዮጵያ ራሷ የምትወከልበት ፊደል አላት። በአሁኑ ጊዜም አማርኛ ብሄራዊ የስራ ቋንቋዋ ነው። ስለዚህ መሪዎቻችን እኛን ወክለው በአለም መድረክ ሲቀርቡ በቋንቋችን መጠቀማቸው የበለጠ የአገራችን መሪ መሆናቸውን የሚያሳይ ነውና።እንደ ፍራንክፈርቱ ባሉ ስብሰባዎች ብሄራዊ ማንነታችንን ትተን ጎሳዊና መንደራዊ ማንነታችንን የምናጎላ ከሆንን ግን አለም ሊያከብረን አይችልም። ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የሚሆነው የጀርመን ጋዜጦች በኖቨምበር 1 ቀን 2018 ዓም እትሞቻቸው ይዘው የወጡት ዘገባ ነው።




ይህ በስክሪኑ ፎከስ ሲደረግ የነበረው ምስል ሲሆን ጋዜጠኛ ተስፋለም ወደየስ ለDW ዜና የተጠቀመበት ነው። አብዛኛውን የኢትዮጵያን ባንዲራ የያዙ ግን በግራና በቀኝ በኩል በርካታ ነበሩ።

እውነተኛ ፎከሱን ለማየት ግን ይህንን አጭር ቪድዮ ይመልከቱ!

https://www.youtube.com/watch?v=gPQiE-xyjo4&feature=share

# እቴ እመይቴ ባንድ

በዶክተር አብይ እና የፍራንክፈርት ከተማ ምክትል ከንቲባን ንግ ግር የተሰማኝን ደስታም ሆነ ተስፋ ከመተንተኔ በፊት ለዛሬ በእቴ እመይቴ የህጻናት ባንድ የቀረበውን ዝማሬ ይዘት በማሳየት ላቁም። ይህ መዝሙር ልብን የሚነካ ብቻ ሳይሆን እኛ ኢትዮጵያውያን ልዩነታችን ውበታችን መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነበር። ህጻናት በተለያዩ የሀገራችን ቋንቋዎች አንድነታችንን ዘመሩ። የፖለቲካ ልዩነታችን የተከፋፈለችና አንድ ልት ሆን የማትችል የተበታተሰች አገር ቢያሳየንም ወደ እውነታውና የህዝባችን ፍላጎት ስንመጣ ግን ልዩነታችን ቀለማችን ነው። አፋርነት፣ ጉራጌነት፣ ኦሮሞነት፣አማራነት፣ ትግሬነት፣ ሶማሊያነት፣ ሲዳማነት፣ ወላይታነት ወዘተርፈ አንዲትና ታላቅ በሆነች ኢትዮጵያ መጽሃፍ ውስጥ የተልያዩ ገጾች ናቸው። አንዲት ገጽ ተልይታ መጽሐፍ አት ሆንም። ገጸ ብዙዋን ኢትዮጵያን ግን አንደኛው ገጽ አይወክላትም።ሁሉም ገጾች የራሳቸው ቦታ አላቸው፤ አንድ ላይ ሲሆኑ ታላቅ ተገልጾ የማያልቅ መጽሐፍ ናቸው ። ያም ኢትዮጵያ ነው። እነዚህ ህጻነት በህብር ኢትዮጵያን አሳዩን። እውነትን መናገር ስላለብኝ ህጻናት እየዘመሩ የምንናፍቃትን አትዮጵያን በምስል በመድረክ ስራቸው እያሳዩን እያሉ ልቆጣጠረው የማልችለው እምባየ በጉንጮቼ እየፈሰሰ ነበር። አዳኝ ካሜራዎች ቢያገኙኝ ኖሮ የሳምንታት የማህበራዊ ሚዲያ ማስመሪያ እሆን እንደነበር ምንም ጥርጥር የለውም። ደግነቱ ተቀምጬበት የነበረው ቦታ የኦነግን አርማ ከሚያጎላው ፎከሱ በተቃራኒ ስለነበር እድል አልነበረውም።በመሰረቱ ህጻናትን ያሰለጠኗቸው ታላላቅ ሰዎች ቢሆኑም

በመጽሐፍ ቅዱስ ''ህጽናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው'' ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ ትዝ አለኝ። በመጨረሻም አንዲት የኢትዮጵያን ባንዲራ የለበሰች ህጻን በሌሎች ህጽናት ታጅባ ኢትዮጵያ ሆና ወደ መድረኩ መጣች ። ሁሉም ህጻናት ከበቧትና ''ኢትዮጵያ ሃገራችን '' የሚለው ዝማሬ ተዘመረ።ለእኔ ይህ የመድረክ ፐርፎርማንስ ከየትኛውም የእልቱ ዝግጅት የተሻለና በአንድነት እንነሳ ነገንም እንገንባ የሚለውን ሃሳብ የሚያጎላ ነበር። የሚያምርብን አንድነት ነው። የሚያስከብረን ታሪካችንን ማዎቅ ነው። ሌሎች እኛን ለመሆን እየናፈቁ እኛ ማንነታችንን ለመካድ የምንጥርበት ፖለቲካዊም ይሁን ማህበራዊ ፍላጎት አይገባኝም።

የፍራንክፈርት ምልከታየን አላበቃሁም ፣ በተለይም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ንግግርና የፍራንክፈርት ምክትል ከንትባን ንግግር ይዘት እመለስበታለሁ። ለዛሬ ግን የጠቅላይ ሚኒስቴሩን አንድ ልብ የሚነካ በዎቅቱ ካደረጉት ንግግር ልዋሳቸውና ላብቃ። '' ኢትዮጵያ ደከማ ይሆናል እንጂ አልወደቀችም እማምየ............''

ህዳር 2018

© አዲስ ተሰፋ